67. ሀሬ ዮይ ስዩቴነን ዋሶይ ስዩቴስ

. አህያ መምጣቱ ሳይሰማ ጩኸቱ ይሰማል

.. ፍየል ከመድረሷ ቅጠል መበጠሷ

68. ሀሬ ደፎይ ዱጥን ፐንዴስ

. አህያ መጫኛው እስከ ሚበጠስ ያራል

.. በሰው ቁስል እንጨት ስደድበት

69. ሀሬ ጫነይ ደረስ ጊድ ዋሱወው ቢድ ድድጋይን ዩስ

. አህያ ጭነት በዛብኝ ብሎ አቤቱታ ሄዶ መጣያ (አላል) አስጨምሮ ይመጣል

.. አላርፍ ያለች ጣት አር ጠንቁላ ትመጣለች

.. አተርፍ ባይ አጉዳይ

70. ሀሮይ በይነ ዴንዶይ ጣዘን ዎዴስ

. መሰረት የሌለው የፍላጐት መነሳሳት ብጤዛ ይቀዘቅዛል

.. እፍ ቢሉ ጭልጥ

71. ሀሮዴ ሀኔ ጌስ፣ ፐርሱዋ አግዮ ዎዴ ጌኔ ጌስ።

. ሌላ ጊዜ አንቺ ይላል፣ ጠላ ስትጠምቅ እሜቴ ይላል

.. ለተሾመ ይሟገቱለታል፣ ለተሻረ ይመሰክሩበታል

.. ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ

72. ሀሰዩነ ጌሬሰይ ዛረሸን ሜቴስ

. ያላሰቡት ቀረርቶ ሲመልሱት ያስቸግራል

.. ከአፍ ከወጣ አፋፍ

.. ሳያውቅ የተረተ ሳይዘራ ያመረተ

73. ሀሶ አሰው ሰሮ ያግን ዩለ ዝንአስ ገውሱ

. እዚህ ቤት ቢሉ ወልጄ ተኝቻለሁ ትላለች

.. ሀራምባና ቆቦ

.. ፍየል ወዲያ ቅዝምዝም ወዲህ

74. ሀሹ ጌነ እመተይ ላፑን ቀማ አቂስ

. እሰይ የማይሉት እንግዳ ሰባት ቀን ያድራል

.. የፈሩት ይደርሳል የጠሉት ይወርሳል

75. ሀሹ ጌነ እመተይ ተመ አች አዴስ

. እሰይ የማይሉት ሰው በእርምጃ እሳት ዳር ይመጣል

.. የፈሩት ይደርሳል የጠሉት ይወርሳል

76. ሀች ከለ ማደ ተነ ዛረ አይቾፐ ጌስ አገነይ

. ዛሬ ጠግበሽ በልተሽ ሌላ ጊዜ አትጠይቂኝ ይላል ባል

.. ተሹሞ ያልበላ ሲሻር ይቆጨዋል

77. ሀቺሮ ቆፓፐ ዎነ ግዮ ቦረ ኑ ሹክድ ሚዶ ቀማ ቆፐ

. የዛሬን ሳይሆን ወኖ የተባለ በሬ አርደን የበላንበትን ቀን አስብ

.. ቀን ያልፋል እስኪያልፍ ያለፋል

.. ሰውን ማመን ቀብሮ ነው

78. ሀችስ ኬሀ ግዮጋፔ ዎንቶስ ኬሀ ግስየባ ኦተ

. ለዛሬ ደግ ነው የሚባለውን ትተህ ነገ ደግ ሊያስብል የሚችለውን ስራ

.. መልካም ስራ ትዞራለች አብራ

.. ስም ከመቃብር በላይ ይውላል

79. ሀችስ ጊዶጌ ሀሮዴዮ ግዴስ

. ለዛሬ ያሉት ለሌላም ቀን ይሆናል

.. የኖረ ያገለግላል

.. ያኖሩት እንቅርት ያገለግላል

80. ሀነ ማተ ኮሸ ግዱኩ ሌሄ ኮሸ

. ይህቺ ሳር ፍለጋ ሳትሆን ዱባ ስርቆት ነች

.. ሊበሉ የፈለጓትን አሞራ ይሏታል ጅግራ

.. ይህቺን ክርክርሻ ዳቦዬን ለማንሻ

.. የዘፈን ዳርዳሩ እስክስታ

81. ሆነ አይበ ዱረይ ግን ሶን ዴእያሮ ቤአርኪ ማዮይ ጠይን አታሮ

. ይሀቺ እንዴት ትጨፍራለች ቢሉ እቤት ልብስ አጥታ የዋለችውን ባየህ

.. አባይን ያላየ ምንጭ ያመሰግናል

82. ሆነ አይበ ዱርሰ ዱረይ ግን ሶን ማዮይ ድግን አትዳሮ ቤአርኪ ጌስ

. ይሀቺ እንዴት ትጨፍራለች ቢባል ልብስ አጥታ እቤት የቀረችውን ባየህ ይላል

.. አባይን ያላየ ምንጭ ያመሰግናል

83. ሆነነ ሆልተኔ በከነ አይሳ ሻከ ትዬቶሶነሸን አመርስ ገለ በከነ ሰንተን ወሬቶሶነ

. ሃናኔና ሃሊቴ የአምስት ሳንቲም ቅቤ ተካፍለው ሲቀቡ ውለው ወደ ማታ በአምስት ሳንቲም ጐመን ይጣላሉ

.. የማይተማመኑ ጓደኛሞች በየወንዙ ይማማላሉ

.. አጉል ፍቅር ያመናቅር

.. የማያዛልቅ ፀሎት ለቅስፈት

84. ሆንቄት ኡትን ቱኬ ፔንትኬ ጌስ

. አኩርፈው ከተቀመጡ ቡና አልፈላም ይላል

.. ወስፌ ከለገመ ቅቤ አይወጋም

85. ሆንታራ ከሉዋፔ ሰሮ ነምሰይ ሎአ

. ከኃይለኛ ቁንጣን ረሃብ ይሻላል

.. ማር ሲበዛ ይመራል

.. ከጮማ ብስና ጐመን በጤና

86. ሆንታራ ኩሼ ሀግሸ ሊጵያ በቄስ

. የተንኮለኛ ሰው እጅ የሰላቢን ራስ ይመታል

.. አለማረፍ ጣር ያበዛል

.. አላርፍ ያለች ጣት አር ትጠነቁላለች

87. ሀንቻኖ አያነይ እሳረ ቤቴስ

. የሃንቻኖ ውቃቢ ኢሳራ ይኰበልላል

.. አልሸሹም ዘወር አሉ

88. ሀንክ ሀንካ ዛሬናጋ ሀርጌ አይቆ

. ወቅታዊ ፍላጐትን የማያረካ በሽታ ይያዘው

. ለጥምቀት ያልሆነ ቀሚስ ይበጣጠስ

89. ሀንደን ምዮ ሀለኩዋ አትደ ኡራ አ አ ነገረይ አይቾ

. እንደዚህ የሚበላውን ‹ሺፈራው› የሰራው ሰው የሱ ጡር ይጠይቀው (ይድረስበት) የእጅህን አትጣ

.. ብድሩ ይድረሰው

90. ሀንግደ ዶነን ባሬቴነ፤ ሀውሁ አትደበን ሾጬቴነ

. በከፈቱት አፍ አይጐርሱም፤ ባነሱት ነገር አይሙቱም

.. ከአፍ ከወጣ አፋፍ

91. ሀኒረ አድዳኮ ሀልተይ ሀልጥስድ አሌነ

. በዚህ ባልፍ ኖሮ ድጡ አይጥለኝም ነበር

.. ላለፈው ክረምት ቤት አይሰራም

.. የፈሰሰ ውሃ አይታፈስም

92. ሀኖ መይ አይቤ? ተመ

ሀኖ መይ አይቤ? ተመ

ያትን አይብስ ሀ ተመይ ሞሳፔ ሽሬተ ዎድኪ?

. ይህቺን ምን በላ? እሳት፣

. ይህቺን ምን በላ? እሳት፣

ታዲያ ለምን ከዚህ በእሳት ከምትበላበት ዘወር ብለህ አትተኛም?

.. ያልተገላበጠ ያራል

93. ሀውሁ ኦትዶበን ሾጮፐ፤ ሀው ጊዶ ዶነን ዛሮፐ

. ብድግ ባደረግከው ነገር አትምታ፤ አፍህ እንዳመጣ አትመልስ

.. አንዴ ከመናገር ሁለቴ ማሰብ

.. ከሆነ ወዲያ ከመናደድ አስቀድሞ ማሰብ

94. ሀውላሾይ ሃተው ደፍን፣ ጠዴ ማተው ደፈስ

. አዞው ወደውሃ ሲስብ፣ ጉማሬው ወደ ሳሩ ይስባል

.. ከራስ በላይ ንፋስ

.. ሁሉም ለራሱ

.. ዘመድ ከዘመዱ አህያ ከአመዱ

95. ሀይ! ተነ ድችደ ደቤ ቡሽር ኩሼ ኤሮ

. ኧረ! ያሳደገችኝ የዘመዴ የቡሽሬ እጅ ይጣለኝ

.. እጅህ ይጣለኝ

96. ሀይሴ ዮሁዋ ዎረነ ጠይኮኔ ሀርግሴስ ጌቴስ

. ምሳሌ ነገርን ባይገድልም ያመነምነዋል ይባላል

.. ነገር በምሳሌ ጠጅ በብርሌ

97. ሀይቀነ ሀነይደ በልቸንተሶ አይያ አዝና አሞተውሱ

. የነባልቻ እናት ልትሞት ስትል ባል ትመኛለች

.. የበላውን ያብላላዋል

.. የለመደች ጦጣ ሁልጊዜ ሽምጠጣ

98. ሀይቀነ ኦሰንችያ መልከታ ቱንንከ ስዩኩ

. የምትሞት አገልጋይ መለከት ቢነፋም አትሰማም

.. የሚፈርስ ከተማ ነጋሪት ቢመታ አይሰማም

99. ሀይቀነ ጊደ ደንገርሳ ሀይተን ላፑን ዘይያ ቱንንከ ስዩነ

. ሊሞት ያለ ዝሆን ጆሮ ሰባት እምቢልታ ቢነፋም አይሰማም

.. የሚፈታ ከተማ አዋጅ ቢነገርበት አይሰማ

100. ሀይቀነ ጊደይ ሀለቃ ጨዬስ

. እሞታለሁ ያለው አለቃን ይሰድባል

.. አይጥ ሞትን ስትሻ የድመት አፍንጫ ታሸታለች

101. ሀይቁወውኔ አይሙወውኔ አው ባወ

. ለሞትና ለህልም ሀላፊ (ዳኛ) የለውም

.. ንጉስ አይከሰስ ሰማይ አይታረስ

.. ሞት ርስት ነው መፈራቱ ለምንድነው?

102. ሀይቁዋ ጠሌ ነኣ፤ ከርሹዋ ጠሌ ጨውለ

. የሞት መድኃኒት ልጅ የመጋኛ መድኃኒት ‹ጫውላ› እንጨት

.. ማር ሸጦ ምን ይገዟል፤ ልጅ ጠልቶ ምን ይወደል

103. ሀይቁዋፔ ዴኦይ ሎኦ

. ከመሞት መኖር ይሻላል

.. ከመሞት መሰንበት

104. ሀይቅን አገናረ ዳፉርን ዬከውሱ

. ሲሞት የምትተው ሲደክም ታለቅሳለች

.. ወግ ነው ሲዳሩ ማልቀስ

.. ትዝብት ነው ትርፉ

105. ሀይቅየ ሀርየን ገለታ ጠዮፒ

. ለሚሞት አህያ ምስጋና አትጣ

.. የሚያልፍ ነገር የማያልፍ ስም ያሰጣል

.. ትዝብት ነው ትርፉ

106. ሀይቅየ ሰውያ ሸሬቹዋ ጌለውሱ

. የምትሞት ጋለሞታ ጠንቋይ ታገባለች

.. አይጥ ሞቷን ስትሻ ስታበዛ ሩጫ፤ ሄዳ ታሸታለች የድመት አፍንጫ

107. ሀይቅያረ ጮይያሮ ሚጨውሱ

. የምትሞት በምታስታውከው ላይ ትስቃለች

.. አመድ በዱቄት ይስቃል

108. ሀይቅደ ሀጥዮ ነአቴ ዴእየ ሂለንቻ ነአይ ኬሀ ጌቴስ

. ከሞተው የሃጢዮ ልጅ ያልሞተው የሰራተኛ ልጅ ይሻላል ይባላል

.. ከሞተ አንበሳ ያለ ውሻ ይሻላል

.. ከመሞት መሰንበት

109. ሀይቅደ ነአ አይያ ተ ነአ ቆሬ ናኡ ወረ ገውሱ

. የሞተ ልጅ እናት የልጁ አንገት ሁለት ክንድ ነው ትላለች

.. ስደት ለወሬ ይመቻል

.. ሩቅ አገር ለውሸት ይመቻል

.. የሞተ ልጅ አንገቱ ረዥም ነው

110. ሀይቅደ ነአስ ቆሬ አዱሰ

. የሞተ ልጅ አንገቱ ረዥም ነው

.. የሞተ ልጅ አንገቱ ረዥም ነው

.. የማያድግ ልጅ በአራስ ቤት ዳንኪራ ይመታል ይባላል

111. ሀይቅደ ነአው በይደ ሜሀያ ዎይቴስ

. ለሞተ ልጅ የጠፋ ከብት ይሸልማል

.. አያስገሳ ኮሶ የት ደርሶ

.. ሞኝ አያውቁብኝም ባይ

112. ሀይቅደ አስ ሱቆ ሱቂ?

. የሞተ ሰው ፈስ ይፈሳል ወይ?

.. የሞተ ሰው ይነሳል ወይ?

.. የፈሰሰ ውሃ ይታፈሳል ወይ?

113. ሀይቆይ ሀልድ ግልቃ ማሬስ

. ሞት ሲስት ከሲታውን ይምራል

.. ለኃጥአን የመጣ ለፃድቃን ይተርፋል

.. የሞት በደለኛ አይያዝ በዳኛ

114. ሀይቆይ ጉታ ጉተነው አምእያ ዎረነ በይስ ጌስ

. ሞት የደኸየውን ለማደህየት ባል የሞተባትን ሴት ለመግደል እሄዳለሁ ይላል

.. በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ

.. ላለው ይጨመርለታል ከሌለው ይወሰድበታል

115. ሀይቆፔ አተነ ገይ አሃ ዶርዮሳ ገኬስ

. ከሞት እቀራለሁ ባይ ሬሳ የሚከመርበት ይደርሳል

.. አተርፍ ባይ አጉዳይ

116. ሀይታ ጩርገ ገወረይ ፐራ ሌጠን ቶጌስ

. ጆሮ ቆራጣ ድመት ፈረስ በሌጣ ይጋልባል

.. ላያውቁሽ ታጠኚ

.. ስንተዋወቅ አንተናነቅ

117. ሀደረ መይ ሀይቂስ

. አደራ የበላ ይሞታል

.. አደራ ጥብቅ ሰማይ ሩቅ

118. ሀደን ግሸው ሀራመ ቱሙዋ መውሱ

. ለሃዳኔ ስትል ሃራሜ ነጭ ሽንኩርት ትበላለች

. ለሃዳኔ ስትል እርም ያለችውን ነጭ ሽንኩርት ትበላለች

.. በሰበቡ መምሬ ተሳቡ

.. አጉል ፍቅር ያመናቅር

119. ሀድያ ሃተይ ኤፍን ደንጩዋ ጌዱዋ ኦሌስ

. ሱሪውን ውሃ ቢወስድበት መቀነቱን ጨምሮ ይከታል

.. እልህ ምላጭ ያስውጣል

120. ሀዴ በይነ ኡረው ሀንቆይ ባ

. ወኔ የሌለው ቁጣ የለውም

.. ለማኝና ሰይጣን የሰጡትን ይቀበላል

121. ሀጋ መለ ኡቴተይ ኑሶን ኮሻ ኤሄስ ጌስ ጌሌሾይ

. እንደዚህ ያለ መቀመጥ እቤታችን ረሃብ ያመጣል ይላል ዝንጀሮ

.. መቀመጥ መቆመጥ

.. ያልተገላበጠ ያራል

122. ሀጌ መጨቴቴየ? ጊን ዎን ከሬ ዱኔ! ገውሱ ጊደ

. ይኸ የሴት ብልት ነው እንዴ ቢል ዱሮስ የደጅ ጉብታ መሰለህ! እንዴ አለች ይባላል

.. ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ

123. ሀጎ ኔ ሱቀይ? ጊን ሀጎ ኔ ሱልአይ? ጌስ ብተኔ

. አንተ ትፈሳለህ? ቢለው አንተስ ታገነፋለህ? አለው ሰውዬው

.. ዝንጅሮ የራሷን መላጣ ሳታይ የልጇን አይታ ትስቃለች

.. ይሉሽን በሰማሽ ገበያም ባልወጣሽ

124. ሀጎ ኔነ ኔ ጎደይ መይዜኔ ጊን በርዮ ጠይን ተነ ዛሴሽን ተነ አውፔ መይዘኔ ጌስ

. አንተ ሰው ጌታህ ልብስ አያለብስህም? ቢለው ለራሱ አጥቶ እኔን እያስማማኝ ነው ከየት አምጥቶ ያለብሰኛል ይላል

.. አባይ ማረፊያ የለው ግንድ ይዞ ይዞራል

125. ሀጎ ኦግየን ኡተይ? ግን ኔ ሶን ጎስየን ኡተይ? ጌስ ብተኔ

. አንት መንገድ ላይ ታራለህ? ሲለው አንተ ቤት በቅል ትቀመጣለህ? አለ ሰውዬው

:: ክፋሽ የተክፋሽን ልብ ቢያውቅ ዋፎ ከቤቱም ባልወጣ ነበር

126. ሃሁወን ዴእየ ደቡዋፔ መተን ዴእየ አለገይ ኬሀ

. ሩቅ ካለ ዘመድ ቅርብ ያለ ባእድ ይሻላል

.. ከማያውቁት መልአክ የሚያውቁት ሰይጣን

.. ከሩቅ ዘመድ የቅርብ ጐረቤት

127. ሃሁዋጌ ሺቅ ገትዮ ገድያ መተይ ኦት ሜስ

. የሩቁ የሚሳልበትን የቅርቡ አርሶ ይበላል

.. ከአብሮ አደግ ጋር አትሰደድ

.. አብሮ ማደግ ያናንቃል

.. አወቅሁሽ ናቅሁሽ

128. ሃሆይ ሶቅየው ጊገ

. ርቀት ለስብቀት ያመቻል

.. ስደት ለወሬ ይመቻል

129. ሃሆይ ሺቅዮ ሶሁዋ መተይ ኀዬስ

. የሩቁ የሚያመልክበትን የቅርቡ ያርሳል

.. የዝቋላን ተራራ የሩቁ ሲሳልበት የቅርቡ ያርሳል፣

.. በእጅ ያለ ወርቅ ከመዳብ ይቆጠራል

.. ነቢይ ባገሩ አይከበርም

.. ያንዱ አገር መልከኛ ሌላ አገር ገባር

.. የቅርብ ጠበል ይሆናል ልጥ መንከሪያ

130. ሃሆይ ቀንግ ገትዮ ቢታ መተይ ኀይ ሜስ

. የሩቁ የሚሳልበትን የቅርቡ አርሶ ይበላል

.. አወቅሁሽ ናቅሁሽ

.. አብሮ ማደግ ያናንቃል

.. ነቢይ ባገሩ አይከበርም

131. ሃረይ ሀረሳ ምን ሃሬናጌ አይፌ ሀንዳ ሜስ

. ያረባው ሌላ ስጋ ሲበላ ያላረባው ፋቂ የአይን ስብ ይበላል

.. ጩኸት ለቁራ መብል ላሞራ

.. አህያ የሚነውን ፈረስ ይበላል

132. ሃሬነ አጣሬ አይፌ ሀንዳ ሜስ

. ያላረባ ልኳንዳ አራጅ አይን የሆነውን (ጮማ) ይበላል

.. በሬ የለፋበትን አህያ ያፍሳል

.. ይታደኋል እንጂ አይታገሉም

133. ሃሰየይ አመኔቴነ፣ ሃተይ ጩጩሜቴነ

. ንግግሩ አይታመን፣ ውሃ አይጨበጥ

.. ነገሩን ያመነና ጉም የዘገነ አንድ ነው

.. የፖሊስ ዘመድ የቤንዚን አመድ የለውም

.. መያዣ መጨበጫ የሌለው

134. ሃሰየይ ውርዶ እመተይ ሀ ከና ጎይነይ ቀንጦ? ጌስ

. ወሬው ያለቀበት እንግዳ የዚህ ውሻ ጭራ ቆራጣ ነውን? ይላል

.. ስራ የፈታ መነኩሴ ቆቡን ቀዶ ይሰፋል

.. አፍ ስራ ሲፈታ ወዳጁን ያማል

135. ሃሰየይ ጋይያረ፣ ሀርጌ አልያረ

. ንግግር ከጋያ ጋር፣ ህመም ከማቃሰት ጋር

.. ነገር በምሳሌ ጠጅ በብርሌ

136. ሃሰያ ሃሰየይደ ነገረው የየ

. ስትናገር ለጡር ፍራ

.. አይመጣምን ትተሽ ይመጣልን በጨመርሽ

137. ሃስ ከቅን ከን ኤኪነ፤ ጦስ እምን አስ ድጌነ

. አርቀው ቢሰቅሉ ውሻ አይነካም፤ እግዜር የሰጠውን ሰው አይከለክልም

.. እግዜር ያደለውን ሰው አያግድም

.. ይታደኋል እንጂ አይታገሉም

138. ሃሽዮ ዎዴ ሀርግያረ ጎርፐዮ ዎዴ ፐጠውሱ

. ሲፍቂ የምትታመም ሲያዋህዱ ትድናለች

.. ይሉኝ አይል የኋላውን አያይ

.. ሞኝ አያውቂብኝ ባይ

.. ቱሪናፋ ቱሪናፋ፣

ከጦር ሜዳ አትገኝ ከምግብ ገበታ አትጠፋ

139. ሃተን ሙነቅዮ ዴሬ ኢተ ጋደ ጩቸን መነቅዮ ዴሬ ገከውሱ

. በውሃ የሚያቦኩበት አገር መጥፎ ነው ብላ በምራቅ ከሚያቦኩበት አገር ደረሰች

.. ግፍ መስራት በልጅ ልጅ ይደርሳል

.. አተርፍ ባይ አጉዳይ

.. የውሃ ግፍ በዕድፍ ውሃ ያስታጥባል

140. ሃተው ነአ ጊርያጌከ ገድየው ሸሉዋ ጊርያጌከ በሪጌ ሎኦ ጌስ

. ለውሃ ልጅ የሚገብርም ለመሬት ገንዘብ የሚገብርም የራሴ ይሻላል ይላል

.. ከማያውቂት መልአክ የሚያውቂት ሰይጣን

.. ኑሮ ካሉ መቃብር ይሞቃል

.. ያላዩት አገር አይናፍቅም

141. ሃተው ነገራ ኦትን ሸፌ ዋይስዮሳ ገቴስ

. በውሀ ጡር ቢሰሩ አሸዋ እሚቸግርበት ያደርሳል

.. የውሃ ጡር በእድፍ ያስታጥባል

142. ሃተው አቅዮ ሶሆይ ባወሸን ምታ ኤከ ዩዩስ

. ውሃ የሚያድርበት የለውም ግን እንጨት ይዞ ይዞራል

.. አባይ ማረፊያ የለው ግንድ ይዞ ይዞራል

143. ሃተይ መልኤነኔ ጩሜነኔ

. ውሃ አይጣፍጥም አይመርምም

. የግመል ሽንት አይገማ አይሸት

144. ሃተይ ሚጭሽን ሜስ

. ውሃ እየሳቁ ይበላል

.. ውሃ እያሳሳቀ ይወስዳል

.. ውሃ ሲወስድ እያሳሳቀ ነው

145. ሃተይ በው አቀነሳ ኤሬነሽን አይበው ሹቻኔ ምታኔ ኤፊ?

. ውሃ የሚያድርበትን ሳያውቅ ለምን ድንጋይና እንጨት ያግዛል?

.. አባይ ማረፊያ የለው ግንድ ይዞ ይዞራል

.. አንቃ ለራሷ አትበቃ ለሰው ጠበቃ

.. መርፌ የራሷን ቀዳዳ ሳታይ የሰውን ትጠቅማለች

146. ሃተይ ቶአነው ቆፐድ ከና ሜስ

. ውሃ ሊጠፋ ሲያስብ ውሻ ይበላል

.. እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል

147. ሃተይ አይብስ ዋሲ ግን ሹቸይ ዋስሴስ ሹቸይ አይብስ ዋሲ ግን ሃተይ ዋስሲስ ጌስ

. ውሃ ለምን ይጮሃል ቢባል ድንጋይ ያስጮኸዋል፣
ድንጋይ ለምን ይኸሃል ቢባል ውሃ ያስኸኸዋል አለ

.. የዛሬ ገበያ እንዴት ዋለ ቢሉ አንዱ ባንዱ ሲስቅ ጀንበር ጥልቅ

148. ሃተይ አይፍየን ቶእን ሽፍየን ኮዩስ

. ውሃ ምንጩ ላይ ሲደርቅ ደለል ይፈልጋል

.. ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ

.. ያልሰማ ሞኝ ነው ጅልሽ ወዳጇ ነው

149. ሃተይ አፈላ ኤፍን ደንጩዋ ጌዱወ ኦሌቴስ

. ውሃ ሸማውን ሲወስድ መቀነቱንም ይጨምራል

.. ክፉ የከፋ ዕለት ቢስ የባሰ ዕለት

150. ሃታ ቀራ ሃት ሜስ

. ዋናተኛውን ውሃ ይበላዋል

.. የላጭን ልጅ ቅማል በላው

.. ስታቦካ ውላ ባተላ

151. ሃታ ትክደ ጣርያ አዋኔ ተማኔ ሆአይደ ፔእደ ቱስዮ ተነ ሳሜስ ሃታ ኡሽ ገውሱ

. ውሃ የቀዳች ገንቦ ዐሐይና እሳት ስትሞቅ የዋለችውን ምሰሶ ውሃ ጠምቶኛል አጠጪኝ ትላለች

.. የበላን ያብላላዋል

152. ሃታ ነገረይ ጨቸን ሙነቅዮሳ ገቴስ

. የውሃ ጡር ዱቂት በምራቅ እሚያቦኩበት አገር ያደርሳል

.. የውሃ ጡር በእድፍ ያስታጥባል

153. ሃታኔ ማላኔ ለጌቴነ

. የውሃና የጨዋ ሰው ክፉ የለውም

.. እሳት ካየው ምን ለየው

.. የአባት ባለጌ የበርኖስ አሮጌ የለውም

154. ሃክን መትን ሃለ ውሸዬ፣ ዴጥን ከውይን ፐረ ጎንደሌ

. ብትርቅ ብትቀርብ ሃላ ውሻዬ፣ ቢከብድ ቢቀል የፈረስ ጋሻ

.. ቢያስቀዝንም ጮማ ይሻላል

155. ሃኮ ግን ሀድሬስ፣ ቆተ ግን ተነ ጌስ

. ራቅ ሲሉት ግራ ይሆናል፣ ተደበቅ ሲሉት እኔ ነኝ ይላል

.. አይጣል ይኋል እንጂ ከጣለ ምን ይኋል
ከመቀነት ወጥቶ ብር ይኮበልላል

156. ሁርቀ ሀርያ ኩጰ ሀርያ ዩለውሱ

. አጭር አህያ ድንክ አህያ ትወልዳለች

.. ያልዘሩት አይበቅልም

.. ግም ለግም አብረህ አዝግም

157. ሁጽያ ሜድየጋ ነኣ ጨቸይ ሜስ

. ፀጉር የሚላጨውን ሰው ልጅ ቅማል ይበላል

.. የላጭን ልጅ ቅማል በላው

.. የአባይን ልጅ ውሃ ጠማው

158. ሁጼ ባወሽን በጠርያ ሸመውሱ

. ፀጉር ሳይኖራት ማበጠሪያ ትገዛለች

.. ያለ አንድ የላት ጥርስ፣ በዘነዘና ትነቀስ

.. ሲሉ ሰምታ ዶሮ ታንቃ ሞተች

159. ሁጼ ቦኢይ ትዬትኮከ ሸጬነ ሚዴትትከ ሞኬነ

. መላጣ ራስ ቢቀቡትም አይወዛ ቢላጩትም አይበቅል

.. ውሃ ቢወቅጡት እምቦጭ

.. ክንቱ ድካም

160. ሀረይስደ ጥርሱዋ አሰንችያ አሀውሱ

. ጠላ ሲረክስ ሰራተኛ በዱቤ ይጠጣል

.. እንካ ያሉት ነገር ይረክሳል

161. ሀርከን ኡይየ ዶጋ ቆሞን ዴእየ ጋሞይ ቀውሃታ አርቀዮጥ ጌስ

. ከታች የሚጠጣን ድፍርሳ ከላይ የሚጠጣ አንበሳ ውሃን አታደፍርስብኝ ይላል

.. አየጅብ ሳታመሃኝ ብላኝ አለ

162. ሀርከን ከልሌናኜ ከልን ዬሬስ

. እታች የማያረካ ከላይ ይሰማል

.. የማያጠግብ እንጀራ ከምጣዱ ያስታውቃል

.. ይህ ሌላ ያ ሌላ

.. ላይጠቅመኝ ጭኔን አረጠበኝ

163. ህርገይ ላቴስ

. የጠረጠረ ይወርሳል

.. አይመጣም ን ትተሽ ይመጣልን በጨመርሽ

.. ያልጠረጠረ ተመነጠረ

164. ህርጎረ ላቶሮ ግደውሱ

. መጠርጠርና መውረስ አንድ ናቸው

.. የፈሩት ይደርሳል የጠሉት ይወርሳል

.. ያልጠረጠረ ተመነጠረ

165. ህችር ህትት አሰ ሚሽ ቦለ

. እችክ እትትት በሰው ገንዘብ

.. ህፃን ልጅና ለማኝ በሰው ገንዘብ ያለቅሳሉ

166. ህነከ ህኖሽን ማታ ገታረከ ቦዬ

. የሆነው ይሁንና ለወተት ያበቃው (ቦዬ) ምግብ ነው።

.. ስሩን የጠላ እራሱን ጠላ

.. አትኩራ ገብስ ጐመን ባወጣው ነፍስ

167. ህዬሰው ቶርጨ ፓሽ

. ለድሃ ሽንፍላ የሽንጥ ስጋ ነው

.. ለይቶት አባ ንጉስዋ

168. ህዬሰው ፑሱዋ እመ ጦሰይ ጡጉንታ ድቼስ

. ለድሃ እከክ የሰጠ አምላክ ጥፍር ያሳድግለታል

.. እከክ የሰጠ ጌታ ጥፍር አይነሳም

.. እግዜር የከፈተውን ጉረሮ ሳይዘጋው አያሳድርም

169. ህዬሰይ ቆትን ኤጨሬ ዴሜስ

. ድሃ የደበቀውን አይጥ ያገኛል

.. የድሃ ጠላት ብዙ ነው

.. የለማኝ ለማኝ ቁርንጮዬን ቀማኝ

170. ህዩሰይ አሹዋ ሚቴ ጊድ ናቱስ ባጫ እሜስ

. ድሃ ስጋ ብሉ ብሎ ለልጆች ማጭድ ይሰጣል

.. አያውቅ ቢዳኝ ከቤቱ ይናኝ

171. ህዩሰይ አይሙወን ፕላ ሜናኮ ከበሸይ አሺ?

. ድሃ በህልሙ አይብ ባይበላ ችጋር ያኖረው ነበር?

.. ድሃ በተስፋ ይኖራል

.. ድሃ በህልሙ ቅቤ ባይጠጣ ኖሮ እከክ ይወርሰው ነበር

172. ህዩሰይ ድጨ ግን ዜጶቴስ

. ድሃ እደግ ቢሉት ይንጠራራል

.. ድሃ ጥጋብ አይችልም

.. ድሃ ሲቀማጠል ከወገቡ ቅምጥል

.. ድሃ ሲንቀባረር ያለቀሰ ይመስላል

173. ህዩሰይ ገጠን ዱሬስ

. ድሃ ከዳር ይጨፍራል

.. ምክር ከድሃ ቤት ግን ማን በሰማት

.. ውሃ የጥቅምት ነበርሽ ማን በጠጣሽ

174. ህዩሰይ ጮይዮ ዎዴ በርከ በ ትራ ኦይቄስ

. ድሃ ሲያስመልሰው ራሱ ደረቱን ይይዛል

.. ምን ያግሳ ውሃ፣ ምን ያምጣ ድሃ

.. አቅምን አውቆ መኖር

175. ህዩሰይኔ ህረይሶይኔ ገይቴነ

. ድሃና እርካሽ ገበያ አይገናኙም

.. ድሃና ገበያ አይገናኙም

.. የድሃ ነገር ምኑም አያምር

176. ህዩሳ ሞቶይ ይግባ

. የድሃ ሙግት ይግባኝ ነው

.. እውር ቢሸፍት ከጎር አያልፍም
.. የቅማል ስደት ከራስ ወርዶ አንገት

177. ህዩሳ ሺምፖይ ዱልያረ ክዩስ
. የድሃ ነፍስ በቂጡ ይወጣል
.. ድሃን አይቼ አይኔን አመመኝ

178. ህዩሳ ናቅየ ኡረይ ጦሳ አይፍየን ጥንቁዋ ዮዴስ
. ድሃን የሚጨቁን ሰው በአምላክ አይን ውስጥ ስንጥር ይሰዳል
.. ድሃን መበደል እግዜር አይወድም
.. ድሃን ሲያስለቅሱ ከስላሴ ይወቀሱ፤
መንግስተ–ሰማያትን አይወርሱ
.. ድሃን ካስለቀሱ በስላሴ ዘንድ ይወቀሱ

179. ህዩሳ ከሎይ ኡዱላ ፑግሲስ
. የድሃ ጥጋብ ሙቀጫ ያስነፋል
.. ድሃ ጥጋብ አይችልም
.. የጠገበ ሰው ራሱን አያውቅም

180. ህዩሳ ኩርኩምየበይ ደራፔ ክዩስ
. ድሃን የሚኩረኩም ነገር ከጥሻ ይወጣል
.. ለደካማ ጌታ አይጠፋውም
.. ለድሃ ሁሉ ጌታው

181. ህዩሳ ይምፐየ ጦሰይ ዘዋ ኤርየ ጭማ ዎሬስ
. ድሃን የሚበድል አምላክ ወሰን የሚያውቀውን ሽማግሌ ይገላል
.. በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ

182. ህዩሳ ዱሌ ጉሱዋ ደንደዩኑ
. የድሃ ቂጥ ቅዘን አይችልም
.. ውሻ ሆድ ውስጥ ቅቤ አያድርም

183. ህዬሳ ጦሰይ ላፑን

. የድሃ አምላክ ሰባት ነው

.. እከክ የሰጠ ጌታ ጥፍር አይነሳም

.. ድሃ በተስፋ ይኖራል

184. ህዬሳ ፐትያ ባሸ ባተሽን ሜደኔ ባሻ ሞትየ ሆሸ ደደሽን ጸልቀኔ

. ለድሃ የቆመውን ባሹን ጋን አይደለ አንጠግነው ባሹን የሚሞግት ሆሹን መብረቅ አይደለን አንሰነጥቀው

.. ጉልበቱ የሌላት ወይዘሮ ገደል የሌለው ዝንገሮ

185. ህዬስ ናቅዮባኔ ፑቶይ ዴጥዮባኔ አስ ኤሬነ

. ድሃ እንደሚበድልና ጥጥ እንደሚከብድ ሰው አያውቅም

.. የአህያ ውሃ ጠጪ

186. ህዬስ ጠዬነ አጮት ጣዬቲስፔ አትን

. ሰው በድህነት አይጠፋም በባለፅዳነት እንጂ

.. የሰው በልቶ አያድሩም ተኝቶ

187. ህዬስያ ከለደ ሀይቀደ አቀውሱ

. ድሃ ከጠገበች ሙታ ታድራለች

. ድሃ የጠገበች ዕለት ሙታ ታድራለች

.. እርሚን ብታፈላ ጋን ሙሉ አተላ

188. ህዳሬ እርኔ ዬለገ ዳነይኔ ቆሄነን አጊነ

. የህዳር ዝናብና ወጣት ሹም ሳይጉዳ አይተውም

.. የጉበዝ ሹም የህዳር ጉም አገር ይደርግም

189. ሂለንቸ እመታ ሞይስን ዎሰንቸ እመተይ ዬስ

. የፋቂን እንግዳ ሲሸኙ የለማኝ እንግዳ ይመጣል

.. ጅብን ፈርቼ ከዋሻ ብወጣ ነብር ጠበቀኝ

190. ሂለንቸይ ገልባ ቃቸይ እጥን ከና ጨዬስ

. ፋቂ ቆዳ መፋቅ ቢያቅተው ውሻ ይሰድባል

.. አህያውን ፈርቶ ዳውላውን መታ

191. ሂለንቸይ ጨፉግድ ኮንችያ ሜዴስ

. ሸክላ ሰሪ ሲያረጅ የትምባሆ ማጤሻ ይሰራል

.. ወታደር ሲያረጅ አቃቢ ይሆናል

192. ሂለንቻ ናት ምታ ሁጵያ ክዮሶነ

. የወጌሻ ልጆች ከዛፉ አናት ላይ ይወጣሉ

.. ጌታዋን የተማመነች በግ ላቷን ውጪ ታሳድራለች

193. ሂላ ደሮይ ካታ ጉጬስ

. እጅግ አዋቂ ብልት ይዋግማል

.. እጅግ ብልሃት ያደርሳል ከሞት እጅግ ስለት ይቆርጣል አሮት

194. ሂላ ደሮይ ጠጵዋ ቀንጤስ

. እጅግ አዋቂ ስር ይቆርጣል

.. እጅግ ስለት ይቀዳል አሮት፤ እጅግ ብልሃት ያደርሳል ከሞት

.. አወቅሽ ቢሏት የቄስ ሚስት መጽሐፍ አጠበች

195. ሂተን ምኔነይ ሚ፤ አቆ ኣደ ጌስ

. መኻታ ላይ የማይበረታ ወደከብት በረት እለፉ ይላል

.. የማይሰማ ሰው ልቤን አፈረሰው

.. የቸገረው ብዙ ያወራል

196. ሂት ቁምእዮጋኔ ኪት አትዮጋኔ ጌለ ኣው ኤሬስ

. የመኻታ መቆርቆርንና የቤትን ማፍሰስ የገባ ሰው ያውቃል

.. ያየ ይናገር

.. ማን ይመስክር የነበረ፡ ማን ያርዳ የቀበረ

197. ሄ ቁነው ሂ ዜንከይ እሼ? ጌቴስ

. ለዚያ ለማጣ ያ ቀውላላ ወንድም ነው? አሉ ይባላል።

.. ግም ለግም አብረህ አገዛግም

198. ሄ ነገው ሄ ነርፐይ እሼ? ጌቴስ

. ለዚያ ሞሮ ያ ተንፋላ ወንድሙ ነው? ይላሉ

.. ቢጤ ከቢጤው ጋር ይውላል

199. ሄላም አወይ ኦላ በይስ ጊድ ቢድ ዎረን ፒእድ ኦመርስ ሶ ዩስ

. የሄላሜ አባት ዘመቻ ሄድኩ ብሎ ሄዶ ጫካ ውስጥ ውሎ ማታ ወደቤት ይመጣል

.. ፈሪ ለናቱ

.. ኑሮ በዘዴ

200. ሄምደይ ቡቸ ኤሬስ

. ያገደ ማጨድ ያውቃል

.. ከባለቤቱ ያወቀ ቡዳ ነው

201. ሄምዳጌ ጠሚስ ግን ሄሜናጌ ጠምቤነ ጌስ

. ያገደው ጠብቷል ሲል ያላገደው አልጠባም ይላል

.. ከባለቤቱ ያወቀ ቡዳ ነው

.. ማን ይመስክር የነበረ ማን ያርዳ የቀበረ

202. ሄሜተነው እጥደ ጌዴ ቀከነው ዴንዴስ

. ለመሪመድ ያቃተው እግር ለመርገጥ ይነሳል

.. ሜዳ መሪመድ ሳታውቅ መሰላል መውጣት አማራት

203. ሄሜተው ክይን ኦጌ ውርኬ ጌስ

. ለጉዞ ሲወጡ መንገዱ አላልቅ ይላል

. ልሂድ ብለው የወጡ እንደሁ መንግድ አላልቅ ይላል

.. ሁሉም ነገር እንዳሰቡት አይሆንም

204. ሄሜታ ደሮይ ጎርዶማ ግየን ገቴስ

. ዙረት የሚያበዛ ከፈንጣጣ መንደር ገበያ ይቆማል

.. አላርፍ ያለች ጣት አር ጠንቁላ ትመጣለች

205. ሄሜታ ደሮይ ጠለህያ ዱቡሸን ገቴስ

. ብዙ መሄድ እሰይጣኖች ጉባኤ ላይ ያወጣል

.. አላርፍ ማለትና መቅበጥበጥ ከፍተኛ ችግር ላይ ይጥላል

.. አለማረፍ ጣር ያበዛል

.. እግር ሄዳ ሄዳ ከአር ጉድጓድ ትገባለች

206. ሄቁምን ተነ አይቆ! ሄድሽን ዎረ! ደራ! ግን ላዌ ግዱወን ሜለ አቴስ

. በስርቅታ እኔን ይነቀኝ! ሲያስነጥሱ ግደል! ትልቅ ሁን ይማርህ! ሲባል ማፋሸግ (ማጋዛት) እመሃል ቤት ይቀራል

.. ጥልቅ ብዩን ውሃ ወሰዳት

.. ልፋቴ ከንቱ

207. ሄቦ ሄረሶን ፐርሶይ ክይን፣ ሄሮ ማረሶን ታዮ ዎዘነይ ኤሬስ

. ሄቦ ሄራ ቤት ጠላ ቢጠመቅ፣ ሄሮ ማራ ቤት ሆኜ ልቤ ያውቃል

.. ከባለቤቱ ያወቀ ቡዳ ነው

.. ልብ አውቃ

.. የአህያን ስባት ጅብ ያውቃል

208. ሄንተይ ቤነሳ ኮቨይ ቤስ

. ክብት ካልታገደበት ለፍለጋ ይኪዳል

.. ላም ባልወለበት ኩበት ለቀማ

209. ሄንታ እጠነ ነአይ እሞሮ ሜነ

. አላግድም ለማለት የፈለገ ልጅ የሰጡትን አይበላም

.. አውቆ የተኛ ቢቀሰቅሱት አይሰማም

.. አያጅቦ ሳታመሃኝ ብላኝ

210. ሄንታ እጠነይ ከታ እጤስ

. ክብት ማገድ እንቢ ሊል ሲፈልግ እህል እንቢ ይላል

.. አያ ጅቦ ሳታመሃኝ ብላኝ

211. ሄንት ገኬነሳ ኮሽ ገኬስ

. ስምሪት አልደረሰበት ፍለጋ ይደርሳል

.. ላም አልዋለበት ኩበት ለቀማ

.. ፍየሏ ወዲያ ቅዝምዝም ወዲህ

212. ሄኪን ሃሰያ ሃሰዬድ ከኤን ከታ ጨኪስ

. የማይጥም ወሬ እያወራ ያልደረቀ እህል ያጭዳል

.. የማይሆን ነገር ለሚስትህ አትንገር

213. ሄኪን እሙተይ ተመ አች ኣዴስ

. ያልፈለጉት እንግዳ እሳት ዳር ይጠጋል

ያልወደዱት እንግዳ እሳት ለመሞቅ ይመጣል

.. የፈሩት ይደርሳል የጠሉት ይወርሳል

214. ሄኪን ዮሁዋ ዮትያጎ፣ ከኤን ጋሽያ ጨክያጎ

. የማይሆን ነገር የምታወራ ያልበሰለ (ያልደረቀ) ጤፍ የምታጭድ

.. የማይሆን ነገር ለሚስትህ አታውራ

215. ሄኪነባ ሃሰይየይ ከኤነባ መጤስ

. የማይሆን ነገር የሚያወራ ያልበሰለ ይለቅማል

.. በማታየው እጅህን አታድርሰው

.. የማይሆን ነገር ለሚስትህ አትናገር

216. ሄኮ ሄ ዮሆይ ቆተ ግን ሄጌከ ኑሶን ፐቴነበ ገውሱ አዘቀ

. ይኸ ድብቅ አይደለም እንዴ ቢሏት እኛ ቤት ግን አሸርባሸር ነው አለች ጭራቅ

.. በእጅ ያለ ወርቅ ከመዳብ ይቆጠራል

217. ሄዙ አቼ ጎደይ ሀመሳ ተው ሀመ ጊስ

. ባለሶስት ጥርስ የታመሰ ጥሬ አምጪ ይላል

.. ትንሽ ያላት እንቅልፍ የላት

218. ሄይ ጊዶበይ ሀረይሴስ

. እንካ ያሉት ነገር ይረከሳል

.. በእጅ ያለ ወርቅ ከመዳብ ይቆጠራል

219. ሄድሼ ግን ኔ ዴኡሰይ ጥንቂስ ገውሱ ምሽርያ

. እንጥስ ቢል ግሳትህ ይቆንሳል አለች ሴትዮዋ

.. ፍየል ወዲያ ቅዝምዝም ወዲህ

.. ሆድ ያባውን ብቅል ያወጣል

220. ሄጋኔ ሄጋኔ ሺሽድ ገዙም ቱክዴ?

. ይህንም ይህንም ሰብስቦ ገዝሙ ቋጠረ

.. መንገድና ገንዘብ ያስማማል

.. የበላይ አደባይ

221. ሆታ ጎዳ ማዴነይ አሰ ኬጠ ጌስ

. ማገርና ግድግዳ የማይረዳ ሰፋ አድርገህ ስራ ይላል

.. በቅሎ ግዙ ግዙ አሞሌ ላያግዙ

.. አፍ ዳገት የለውም

222. ሆታ ጐዳ እሜናኔ ኬታ አሰ ኬጠ ጌስ

. ግድግዳና ማገር የማይሰጥ ሰው ቤቱን ሰፋ አድርገህ ስራ ይላል

.. በቅሎ ግዙ ግዙ አሞሌ ላያግዙ

223. ሆን ጊዶ ፐረይ አፎረ ውሌስ

. ያመኑት ፈረስ ገደል ውስጥ ይገባል

.. ያመኑት ፈረስ በደንደስ

224. ሆኦ ሆምቤ ዘጐሶን በሸያ ሜንቴስ

. የዚያ ቤት የቅብጠታቸው ብዛት የኃለውን ምጣድ ይሰብራል

.. የቀበጠ ሰው ሞትን ይመኛል

225. ሆኦ ሆምቤ ዘጐሶን ግላ ሜንቴስ

. የቅብጠት ብዛት እዚያ ቤት ሰፌድ ያሰብራል

.. የቀበጠ ሰው ከሞት ይደርሳል

226. ሆኮ ዶስያረ አርሰን ጐፌሬተውሱ

. ማጐንበስ የምትወድ አልጋ ላይ ትንፈራገጣለች

.. የማያውቁት አገር አይናፍቅም

.. ላያውቁሽ ታጠኝ

227. ለምእያ ጤለይደ ለምእያ ምተውሱ
. በጕሪጥ እያየች ሳታኝክ ትውጣለች
..አስመሳይ
.. ሰው መሳይ በሽንጕ
.. ሌባ ላመሉ ዳቦ ይልሳል

228. ለንቁወው ዬክየ ናተ መረይ ዬዴስ
. ለምግብ የሚያለቅሱትን ህፃናት ጥጃ ይረግጣል
.. ሆዱን ያለ ሆዱን ተወጋ
.. ለሰበበኛ ቂጥ መረቅ አታብዛበት
.. የተከፋ ተደፋ

229. ለንጩ ላኮንተሶ አይዮ ለኮ ቦይናፔ ሜለ አይሴስ
. ኩርፊያ የላኮን እናት እንስራ ሙሉ ከተቀቀለ ጕደሬ ሳትበላ ያሙዋን ያሳድራታል
.. ከአኩራፊ ይሻላል ሆደ ሰፊ
.. የትቆጣ ራቱ ምሳው ነው

230. ለንጩ ላኮንተሶ አይዮ ፕላፔ አሺድ ሱለው ኤፌስ
. ኩርፊያ የነላኮን ቤት እናት ከአይብ አስቀርቶ ለስቅላት ይወስዳታል
.. አመልና ጭራ ከወደኋላ

231. ለኮ ለንጩ ፕላ ድግ አይሲስ
. ላኰን ኩርፊያ አይብ አስትቶ ያሳድረዋል
.. የተቆጣ ራቱ ምሳው

232. ለይት ሀይቀነ ብተኔ ሀለይት ሱርያ ጦቅስ ግጤስ
. ለከርሞ የሚሞት ዘንድሮ ሱሪውን ከፍ አድርጕ ይታጠቃል
.. ውሃ ሊያንስ ሲል ይገማል ሰው ሊቀልል ሲል ይኮራል

233. ለይት ሀይቀነ ኡሪይ ሀለይት ዱፉዋ ኩወን ኡቴስ

. ለከርሞ የሚሞት ሰው ዘንድሮ እመቃብር ጥላ ይቀመጣል

.. ድሪያ የዝሙት ዋዜማ ነው

234. ለይት ሀይቀነ ኡር ሀለይት ከሬ ጠዴን ዱቡሼስ

. ለከርሞ የሚሞት ከታችኛው በራፍ ላይ ይቀመጣል

.. ለመጪው የሚከዳ ከቤት ወጥቶ ያድራል

235. ለይት ሀይቀነው ሀይለይት ላፈውሱ

. ለከርሞ ልትሞት ዘንድሮ ትከሳለች

.. የዘፈን ዳር ዳሩ እስክስታ

236. ለይት ኮሽተነው ሀለይት ከተ ዶኦን ኤቄስ

. ለከርሞ የሚራብ ዘንድሮ እህል ተራ ያንሾብባል

.. የፈሩት ይደርሳል የጠሉት ይወርሳል

237. ለይት ጎየነ ከነይ ሀለይት ጎይና ሻሬስ

. ለከርሞ የሚያብድ ውሻ ጅራቱን ይቆለምማል

.. ሰው ሊቀልል ሲል ይኩራል፣ ውሃ ሊጠፋ ሲል ይገማል

238. ለግያ ላፈይ ሃታ ፕኒድ ጫቄስ

. የማይሆን ጓደኛ ወንዝ በተሻገረ ቁጥር ይማማላል

.. የማይተማመኑ ጓደኞች በየወንዙ ይማማላሉ

239. ለጌ ዶሰይ ለደ ገዴ ኦቴስ

. ጓደኛ የወደደ ጭንጫ መሬት ያርሳል

.. ይሉኝታ ቤት አይሰራም

240. ለጌ ግሸው ለደ ገድያ ቦሎ ግሸው ቦዘ መቻ

. ለጓደኛ ሲባል ጭንጫ መሬት ለአማች ሲባል ሞኝ ሚስት

.. ይሉኝታ የራስ አሊን ቤት የፈታ

.. ጉሽ ለልጇ ስትል ተወጋች

241. ለጌ ጭመይ ሸየ ደሬስ

. ጓደኛውን ያታለለ አር ይበዛዋል

.. የከፉ ሰው ተገዝካር ያቅራል

.. ሰውን እጐዳ ባይ አመድ ተንከባላይ

242. ለጌቶይ ሀይቅን በመጬቴታ ጎምአረውሱ

. ውሽማዋ ሲሞት እንትኗን ታደማለች

.. ከፈጣሪ ቂጥ ጫሪ

243. ለጽለጽ እንጠርሰይ ቴንጌሬረ ሀይታ በቅሴስ

. ቀለብላባ ምላስ ደሀና ጆሮ ያስመታል

.. ለሃጥአን የመጣ ለፃድቃን ይተርፋል

.. ምላስ በለፈለፈበት ጉንጭ ይመታል

244. ላ ኔነ ሰአን ኤቀደ ጨዶ ምታ ጤራ ከየደ ጨዶ ግን፣ ምታ ጤራ ከየደ ጨዳ ያጌስ፣ አይስ ግን ህን ኬንዮከ ዴአሸነ ጌስ

. አንተ መሬት ላይ ቁሜ ልውጋህ ዛፍ ላይ ወጥቼ ልውጋህ ቢለው ዛፍ ላይ ወጥተህ ውጋኝ ይላል ለምን ቢባል እስከዚያ ድረስ እቆያለሁ ይላል አሉ

.. ማምሻም እድሜ ነው

245. ላ ኔነ ሸሞ? ግን ሄጌ ኔ ሼኔ፣ ቤቱቴ ግን ሄጌ ተ ሼኔ ጌስ

. አንተ ሰው ልግዛህ? ቢለው ፍላጐትህ ነው ትኮበልላለህ? ቢለው ያ የኔ ፍላጐት ነው አለ ይባላል

.. ሙያ በልብ

246. ላ ጠዴን ጠረር ግየይ አይቤ ጌስ ዘሬ

. ኧረ ታች የሚንጣጣው ምንድነው ይላል እንሽላሊት

.. ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ

247. ላሬነ ዴምበን ዱርየይ ናአሽን እሶይ እሱዋ ያ ሺቀ ያጌስ

. ላሬና ሜዳ የሚጨፍሩት ሁለት ናቸው ግን አንዱ አንዱን ወዲያ እልፍ በል ይላል

.. ከተዋደዱ አንድ እንጀራ ለአስር፣
በጠብ ጊዜ አስር እንጀራ ለሁለት አይበቃም

248. ላሾ ናቱ አይፌ ሎኦ ጊሽን ሾሌስ
. የላሽ አካባቢ ልጆች አይን ደህና ነው ሲባል ይንሸዋረራል
.. የዘሬን ብተው ያንዘርዝረኝ

249. ላታ ኤኬና ሾሮይ ብት ዎሬስ
. የማይወርስ ጐረቤት በሟርት ይገድላል
.. አያገባው ገብቶ አያወዛው ተቀብቶ
.. ሆዳም ቢሸከም የበላ ይመስለዋል

250. ላፊ ለግያረ ፐኑወን ፐኑወን ጫቂስ
. ከማይሆን ጓደኛ ጋር በየመሻገሪያው ይማማላሉ
.. የማይተማመኑ ጓደኞች በየወንዙ ይማማላሉ

251. ላፊ ማደይ ይምፖ ኤኬስ
. ለደካማ ያገዘ በጡጫ ይመታል
.. ከአህያ ባልንት የፈረስ ውሽምነት

252. ላፊ ሸንቄ አይቅደይ ከሴት ብርሼስ
. ትንሽ ስንቅ የያዘ አስቀድሞ ይፈታል
.. ትንሽ ያላት እንቅልፍ የላት

253. ላፊ ነእ አች ሜስ
. የማይረባ ልጅ ወትውቶ ይበላል
.. ይሉኝ አይል የኋላውን አያይ

254. ላፊ ናቱ አዋ ቢታ በይዝድ አሹዋ ሞሶነ ጊዮገደን፣
. የማይረቡ ልጆች ያባታቸውን መሬት ሸጠው ስጋ ይበላሉ እንደሚባለው
.. የማትረባ ልጅ ያባቷን ገዳይ ታገባለች
.. የማይረባ ልጅ ከሚወለድ እናቱ ሆድ ውሃ ሆኖ ቢቀር ይሻላል

255. ላፌ አስ አይሳ ማናፔ ፐየ ኡረ ሰንተ ጢጣ ምዮጌ ሎኦ

. የማይረባ ሰው ቅቤ ከመብላት የደህና ሰው ጉመን ጥብስ መብላት ይሻላል

.. ትንሽ ሰው ትንሽ ነው

256. ላፌ አዝነይ ሚዚድ ጨዩስ (ቦሬስ)፣ ጉታ ጉጡኔይ ጉፒዲ ጉንዴስ

. የማይረባ ባል አብልቶ ይወቅሳል

.. ትንሽ ትል ሲዘል ይኮማተራል

.. ትንሽ ሰው ውለታ ይቆጥራል

257. ላፌ ጠልያ ኡይደይ ቶሁዋ መሌስ

. ትንሽ ኩሶ ጠጥቶ በሰላቢ ያሳብባል

.. አያጅቦ ሳታመሀኝ ብላኝ

.. ቀድሞ ነበር እንጂ መጥኖ መደቆስ አሁን ምን ያደርጋል ድስት ጥዶ ማልቀስ

258. ላፌነ ሀተይ ከና ሜስ

. የሚጠፋ ውሃ ውሻ ይበላል

.. ውሃ ሊያንስ ሲል ይገማል

259. ላፌይ ላታ ናጌስ

. ደካማ ሰው ውርስ ይጠብቃል

.. ሰነፍ ቤት አይሰራም

260. ላፌይ ላታ አሞቴስ

. ደካማ ሰው ውርስ ይመኛል

.. አድረው ሊለዩ አመል

.. ሰነፍ ቤት አይሰራም

261. ለፌይ ላጥ ስምድ ወዴስ

. የማይረባ ሰው ምሳውን ከበላ በኋላ ይደበድባል

.. ብር ላበደረ ጠጠር

262. ላፈይ ሲትሽን ውሬስ

. ትንሽ ነገር እየቆጠቡት ያልቃል

.. ፉት ቢሉት ጭልጥ

263. ላፈይ ጣፋወን ከኤስ

. ትንሽ ነገር በማሰሮ ይበስላል

.. ትንሽ ሰው ትንሽ ነው

264. ላፋረ ለጌ ግደናፔ ፐጣረ ሞርኬ ግደነ

. ከማይረባ ሰው ጋር ጓደኛ ከመሆን ከደህና ሰው ጋር ባላጋራ መሆን

.. ከደሃ ከመበደር ከባለፀጋ መለመን

.. የጨዋ ልጅ ሲፋታ የተጋባ ይመስላል

265. ላፋረ ለጌትን ቁንጡዋረ ምዜስ

. የማይሆን ሰው ጓደኝነት ካራራ ጋር ያስበላል

.. የትንሽ ሰው ፍቅር መቀምቀሚያው ጥቁር

266. ላፉ ላጠናፔ ሜለ ብዮጌ ኬሀ ገውሱ

. ትንሽ ነገር ምሳ ከመብላት ባዶ መሄድ ይሻላል ትላለች

.. አሽር ባሽር በልቶ ሆዴን ከማለት፣ ጦም ውሎ ጦም አድሮ ጥሩ መሸመት።

267. ላፑን ለይተ በይራፔ ላፑን ዴሬ ከንትደይ በይረ

. ከሰባት አመት ታላቅ ሰባት አገር ያቋረጠ ታላቅ ነው

.. ያየ ይናገራል የተወለደ ይወርሳል

268. ላፑን ለይተ ገትደ ብተኔ ከሬ ገክድ ዎጤስ

. ሰባት አመት የቆየ ሰው እደጁ ሲደርስ ይሮጣል

.. ሰባት አመት የታወረ ሰው ነገ አይንህ ይበራል ቢሉት ዛሬን እንዴት አድሬ ይላል

269. ላፑን ለይተ ገትደ ዘልአንቸይ ከሬ ገክድ ዎጤስ

. ሰባት አመት የቆየ ነጋዴ እደጁ ሲደርስ ይሮጣል

.. ሰባት አመት የታወረ ነገ ይበራልሃል ቢሉት ዛሬን እንዴት አድሬ ይላል

270. ላፑን ላፈይ ኬጢዶ ኬታ እስ ከነይ ላሌስ

. ሰባት ደካሞች የሰሩትን ቤት አንድ ውሻ ይበታትናል

.. ተልባ ቢንጫጫ ባንድ ሙቀጫ

271. ላፑን ሙገረይ ፐራ ቶግሽን ልሱዋ ኦን እመኔ?

. ሰባት አገልጋዮች ፈረስ ላይ ሲቀመጡ አለንጋ ማን ያቀብላቸዋል?

.. ሁሉም አራሽ ከሆነ ማን ይሸምታል

272. ላፑን ቀንታ ዬለደ አሾ ጎደቴ ጠልያ ኡየውሱ

. ሰባት የወለደች የቡአ መድሃኒት ትጠጣለች

.. ልጅ ወልዶ ልጅ መሆን

.. ለማያውቅሽ ታጠኝ

273. ልሎይ በርዮ ማየነው ባወሽን በር ቁፍያ ሹቻ መይዜስ

. ቢራቢሮ ለራሱ የሚለብሰው ሳይኖረው ክንፉን ድንጋይ ያለብሳል

.. አንቃ ለራሷ አትበቃ ለሰው ጠበቃ

274. ልባምያ በ ቦሎትዮ ቀጠረውሱ

. ብልህ አማቷን ትገርዛለች

.. ለናቷ ምጥ አስተማረች

275. ልባምያ በ ኣይዮ ኦትሰውሱ

. ብልህ ልጅ እናቷን አሽከር (አገልጋይዋ) ታደርጋለች

.. የልጅ ብልጥ እየቀደመ ይውጥ

276. ልባምያ አዬ ኮይታ መውሱ

. ብልጥ የናቷን ጥሎሽ ትበላለች

.. መሸጥ የለመደች እናቷን ታስማማለች

277. ሌሌሄ ምሾይ ምዜነ ዶቾነው ቀስ ናት ገቴነ

. ዱባ ስለሚፋጅ ቶሎ አይበላም እስኪቀዘቅዝ ደግሞ ልጆቹ አያደርሱም

.. ላም እሳት ወለደች እንዳትልሰው ፈጃት እንዳትተወው ልጇ ሆነባት

278. ሌሌሄ ናኡ ቡሌ ሃታ ኡይዮገ ቦይና ሀይተይ ስዮፖ

. ዱባ ሁለት እንኰላ ውሃ መጠጣቱን የገዳሬ ጆሮ አይስማ

.. ጉድ ይገርማል አህያ ከጅብ ይከርማል

.. ጉድ እንግዳ ነገር

279. ሌሌሄ ዬሉዋ ኤረስፔአትን ድቼዋ ኤሬነ

. ዱባ መውለድ እንጂ ማሳደግ አያውቅም

.. ፈጣሪ መግደል እንጂ መቅበር አያውቅም

280. ሌሌሄ ዬልድ ጉዬ ጤሌነ

. ዱባ ወልዶ ወደኋላ አያይም

.. ላያጠግቡ መጋበዝ ላይገድሉ ካራ መምዘዝ

.. የዋልንበትን አረም በላው

281. ሌምሶይ ዮሁዋ ዱተነ ጠይኮኔ ላፌቴስ

. ምሳሌያዊ ንግግር ነገርን ባይቆርጥም እንኳ ያመነምነዋል

.. ነገር በምሳሌ ጠጅ በብርሌ

282. ሌቅዮ መችያ አቱመ ነአ ዬለውሱ

. የናቋት ሚስት ወንድ ልጅ ትወልዳለች

.. የፈሩት ይደርሳል የጠሉት ይወርሳል

.. የናቁት ያስረግዛል

283. ሎሃ ምያረ ብን ቢጣላ ምያረ የውሱ

. ሎኮ የምትበላ ስትሄድ ልጓም የምትበላ ትመጣለች

... የባሰ አለና ሚስትህን አትፍታ

... የባሰ አለና አገርህን አትልቀቅ

284. ሎእነ ግያረ ሎቄተውሱ፣ ባና ግያረ ትስቴታውሱ

. አምራለሁ ያለች ትሽሞነሞናለች፣ እሄዳለሁ ያለች ትቀባባለች

... መሄድ ያማረው ራቱን በጨረቃ ይበላል

285. ሎእያ ከዩወንከ ሎአውሱ

. ቆንጅዋማ በሀዘንም ታምራለች

... ይታደሷል እንጂ አይታገሉም

286. ሎእያ ጉፈንተ ኤፋዳ ጉሴነን ዛረ ኤህያሮ

. ደህና ማለት አዘቅዝቃ ወስዳ ሳታፈስ የምታመጣ ናት።

... የሰው ደህና የለውም

... ሰውን ማመን ቀብሮ ነው

287. ሎኦ ሎማ ጎዳ ሎደን ጤልን ጩወይ ጳሌስ

.. ሸጋውን የሎማን ሹም አተኩረው ሲያዩት ወዙ ያብለጨልጫል

... ነገርን አዳምጦ፣ እህልን አላምጦ

288. ሎይት ግጥን ቀጥድ አንጌስ

. አሳምረው ሲለብሱ ጠልፎ ይጥላል

... ሲያጋጌጡ ይመላለጡ

289. መ መ ጊዳረ ቢት ምዘውሱ

. ብላ ብላ ያለች አፈር ታስበላለች

.. የቸኰለች አፍሳ ለቀመች

.. አላርፍ ያለች ጣት አር ትጠነቁላለች

290. መ ማነ ጠየ ጦሰ ገለቴ፣ ላፑን ዎደላ ቆመ ሎኮሜ

. ብትበላም ባትበላም እግዜርን የምታመሰግን ሰባት ጉረምሳ የምታቅፍ

.. ይታደሷል እንጅ አይታገሉም

291. መ ድገደ አደ ድማየ ዶና ጎደው

. በልቶ የሚያወራ አፍ ያለው

.. በውሻ ሆድ ቅቤ አያድርም

.. አፍ ሲናገር ሆድ ይንቃል

292. መለቀ ዱርሰ ጎበ ግን ቃረ ቤሰውሱ

. ማላቃ ለጭፈራ ጉበዝ ናት ብትባል ገልባ ታሳያለች

.. ምኗ እንደመከሩት

.. የቄስ ሚስት አወቀች ቢሏት መጽሐፍ አጠበች

293. መለን ሀርያ ሱቆይ ቡለ

. በመላ ያህያ ፈስ ቡላ ነው

.. ሳያረጋግጡ ወሬ ሳይገድሉ ጉፈሬ

.. እንዲያው በመላ ፈስ ዳለቻ ነው

294. መለን ሱቆይ ቡለ

. በግምት ፈስ ዳለቻ ነው

.. እንዲያው በመላ ፈስ ዳለቻ ነው

295. መለንቸ ኡንጨው ጠሌቴት ባወ

. ደህና ቆጮ መድሀኒትነት የለውም

.. ዱባና ቅል አበቃቀሉ ለየቅል

296. መለይ መለሌነሽን ሉንተይ መለሎ

. መልኳ ባያምርም ስሟ ቆንጂት ነው

.. መልከ ጥፉን በስም ይደግፉ

297. መለይ በይነ መተይ ተማ ዱኬስ

. የማያስብ ንብ እሳት ይነድፋል

.. አይጥ ሞቷን ስትሻ ስታበዛ ሩጫ ሄዳ ታሽ ታለች የድመት አፍንጫ

.. አለማረፍ ጣር ያበዛል

298. መለይ በይነ ጌሬሰይ ዛሩወን ጦኔስ

. ሳያስቡ የጀመሩት ቀረርቶ ለመመለስ ያስቸግራል

.. ከመናገር ማዳመጥ ከመዋጥ ማላመጥ

.. ከመጠምጠም መማር ይቅደም

.. ከመናገር በፊት ማሰብ

299. መላ ሎእዮ ጎሮሞቴ ሜስ፣ ባሌ ታቦታ ከይሶይ ሜስ

. መልከ መልካሟን ቡዳ ይበላታል፣ የባሌን ታቦት ሌባ ይበላል

.. እዩኝ እዩኝ ያለች ደብቁኝ ደብቁኝ ትላለች

.. አፍ ያበዛ ጥበቡ ዋዛ

300. መላረ ዴእየ ቁማ ከትን መል በይነ አስ ሜስ

. ጥሩ ምግብ ተሰርቶ የማይፈለግ ሰው ይበላል

.. ነገር ያለቦታው ሆነና ቸገረኝ

.. የማይሆን ነገር የተገላብጦሽ ያቺን ላንቺ ማናለሽ

301. መል ምርቂቀሽን ሉንት አዋየ

. መልኩ መጥፎ ሆኖ ሳለ ስሙ አዋዩ ነው

.. መልከ ጥፉን በስም ይደግፉ

302. መል በይነ ከፎይ መል በይነ ምታ ቦል ኡቴስ

. ዘዴ የሌለው ወፍ ቅርንጫፍ በሌለው ዛፍ ላይ ያርፋል

.. መካር የሌለው ንጉስ ያለ አንድ አመት አይነግስ

.. ነገርን አዳምጦ፣ እህልን አላምጦ

303. መልኡዋ ማነ ጋደ ኤጩርያ ዩርዱወን ጌለውሱ

. ጣፋጭ እበላለሁ ብላ አይጥ ሽምቀቆ ውስጥ ትገባለች

.. በሬ ሆይ ሳሩን አየህና ገደሉን ሳታይ

304. መልኡዋ ቤእደ ቁጠርስያ ናአ ስመውሱ

. የጣፈጣት ጀርት ሁለቴ ትመላለሳለች

.. የለመደች ጦጣ ሁል ጊዜ ሽምጠጣ

305. መልኡዋ ቤእደ ኤጩርያ ዩርዱወን ጌለውሱ

. ጣፋጭ ነገር የለመደች አይጥ ወጥመድ ውስጥ ትገባለች

.. በሬ ሆይ ሳሩን አየህና ገደሉን ሳታይ

.. ሆዱን ያለ ሆዱን ተወጋ

306. መልኤት ከትን ጉሱዋረ ክዩስ

. አጣፍጠው የሰሩት በተቅማጥ ይወጣል

.. ሲያጌጡ ይመላለጡ

307. መልኤት ዮትን መተይ ስዩስ

. አጣፍጠው ሲናገሩ የቅርቡ ይሰማል

.. የማይነጋ መስሏት ቋት ላይ አራች

308. መልኤትድ ከትን ጉሰሰድ ዎሬስ

. አጣፍጠው የሰሩት በተቅማጥ ይገላል

.. ሲያጋጌጡ ይመላለጡ

.. አተርፍ ባይ አጉዳይ

309. መልኤነ ቁመይ ሰዎ ኢተ

. የማይጣፍጥ ምግብ በሽታ ያውዳል

.. ቢከፍቱት ተልባ

.. ሰው መሳይ በሸንገሎ

.. በሰም የተቀባ ጥርስ ቢበሉበት አያደቅ ቢስቁበትም አያደምቅ

310. መልኤነ ፐርሱዋ አግዳረ ገንጠ ገንጠ ጤለውሱ

. የማይጣፍጥ ጠላ የጠመቀች እየቀመሰች ታያለች

.. ገልቱ የራሷ ወጥ ይጣፍጣታል

.. ቀድሞ ነበር እንጂ መጥኖ መደቆስ አሁን ምን ያደርጋል ድስት ጥዶ ማልቀስ

311. መልአ ማነ ጊደ ቆሬ መንቁዋ ዬዴስ

. ጣፋጭ እበላለሁ ያለ ጉረሮ ድህነት ያመጣል

.. ሞኝ የዕለቱን ብልጥ ያሙቱን

.. ሆዱን የወደደ ማዕረጉን ይጠላል

312. መልአ ሚደ መጫስያ አዶ ኪሬ ላጨውሱ

. ጣፋጭ መብላት የለመደች ሴት የቦሌ ገንዳ ትልሳለች

.. የለመደች ጦጣ ሁል ጊዜ ሽምጠጣ

313. መልአ ቁመይ ሀርግያ ዛሬነ፣ መጨ ነአ በሱዋ ኡኬነ።

. ጣፋጭ ምግብ ከበሽታ አያድንም፣ ሴት ልጅ ቁራሽ አትጋግርም

.. ዱባና ቅል አበቃቀሉ ለየቅል

314. መልኦኔ መስቀለኔ ናግደይ ሜስ

. ጣፋጭና መስቀል የጠበቀ ይበላል

.. የረጋ ወተት ቅቤ ይወጣል

.. የትዕግስት ፍሬ ጣፋጭ ነው

315. መልአይ ጠርዘ አሼነ፣ መገንጠይ ሸሎ ውርሴስ

. ጣፋጭነት ጉርሻ አያስተርፍም፣ ጉቦ ገንዘብ ይጨርሳል

.. ወይ ጠጅ ገንዘብ ባትፈጅ

316. መልአይ ጠርዘ ድግን፡ ሱሎይ በርሱዋ ድጌስ

. ጣፋጭነት ጉርሻ አላስቀር ሲል ቃጠሎ መጉረስ ይከለክላል

.. ላም እሳት ወለደች እንዳትልሰው ፈጀት እንዳትተወው ልጁ ሆነባት

317. መልአይ ጦንን ናአ ወሬቴስ

. ጣፋጭ ነገር የሰረቀ ሁለቴ ሰርቆ ሁለቴ ይደበደባል

.. የለመደች ጦጣ ሁል ጊዜ ሽምጠጣ

318. መልዱዋኔ ሽምፒላኔ ቁረጸይ ሜስ

. ማሽላና ሽንፍላ የለቀመ ይበላል

.. የትዕግስት ፍሬዋ ጣፋጭ ነው

.. ከመሞት መሰንበት

319. መልዱዋኔ ሺምፒዋኔ ቁረጸይ ሜስ

. ዘንጋዳና ነፍስ የቆጠበ ይበላል

.. መከራና ጉም እያደር ይቀላል

.. መከራን የቻለ አሸናፊ ይሆናል

320. መረ አሹዋ ቦል ሚዜ ኦይሳ ዬጌቴስ

. በጥጃ ስጋ ላይ የናት ቅቤ ይጨመራል

.. በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ

321. መረ ገትደ ማህያ ሾሮ ጠይሰውሱ

. ግልገል ያደረሰች ነብር ጉረቤት ታጠፋለች

.. ከወፈሩ ሰው አይፈሩ

.. ጌታዋን የምትተማመን ውሻ ፍሪዳ ሲታረድ ወደ ወንዝ ትወርዳለች

322. መረጭየን ሚግድ ጉዱፊን ኅርድድ ጊን ጉደሬ አወን ዶአ. ጌነን ዎጤስ

. በአንጀት ተማግሮ በማጅራት ስጋ የተዘጋ ነው ሲባል ጅብ የት ነው ሳይል ይሮጣል

.. ጅብ በአጥንት የተገደገደ በጅማት የተማገረ ቤት አለ ቢሉት ወደ’ት ነው ሳይል ገደል ገብቶ ሞተ

.. መርፌ መግቢያዋን እንጂ መውጫዋን አታውቅም

323. መሩወው መርጮ ቀቼናኄ ድንክያስ ቦረ ቀቼስ

. ለጠንቋይ ትንሽ ገንዘብ የማይሰጥ ለቀብር ቀን ለከበሮ መች በሬ ይሰጣል

.. አልጠግብ ባይ ሲተፋ ያድራል

.. አተርፍ ባይ አጉዳይ

324. መርያ ናአ ዋሰናኔ አይያ እሲቶ ዳሩ

. ጥጃዋ ሁለቴ ከምትጮህ እናትየዋ አንዴ ታጓራ።

.. ልጅ ያቦካው ለራት አይበቃም

.. ከሺህ መካሪ አንድ ቋጣሪ

325. መርፐያ ባጋ ቤኡኩሽን አሰባ ጎርደውሱ

. መርፌ የራሷን ሳታይ የሌላውን ቀዳዳ ትደፍናለች

.. ይሉኝን በሰማሽ ገበያም ባልወጣሽ

.. አንቃ ለራሷ አትበቃ ለሰው ጠበቃ

.. ዝንጀሮ የቂጧን መላጣ ሳታይ በባልንጀራዋ ትስቃለች

326. መርፔ በር ዱልየን ጌልደ ቁንጩትያ ጉቼነሽን ጩርቃ ጩደነው ስንተው ዎጢስ

. መርፌ በቂጡ ያለውን ክር ሳይጐትት ጨርቅ ለመውጋት ወደፊት ይገሰግሳል

.. የሰው ስታማስል የራሷ አረረባት

327. መርፔ አቴነይ መረ በይዜስ

. በመርፌ ክር የማያስገባ ጥጃ ይሸጣል

. በመርፌ ሰፍቶ የማይለብስ ጥጃ ይሸጣል

.. ሞኝ ሰው ቤት አይሰራም

.. ሞኝ የዕለቱን ብልህ ያመቱን

328. መርፔፔ ቀር ባሽን ጦንግን ጨድ ኤሬነ

. ከመርፌ የበለጠ ሹል የለም ግን ቢወረውሩት አይወጋም

.. የጋን መብራት

.. አይን ካላየ ግንባር ነው

329. መሮይ ባስ ኤሬነ

. ጠንቋይ (ቃልቻ) ስለራሱ አያውቅም

.. አንቃ ለራሷ ሳትበቃ ለሰው ጠበቃ

.. ለራሱ አያውቅ ነዳይ ቅቤ ለመነ ላዋይ

330. መሰምየው ተ መጬ አሴ ገውሱ አንገለ ጎደትየ

. ማን ይሙት እኔ ሴት ነኝ አለች የአንገላቲ እመቤት

.. የሴት ወንድ ነኝ እንደማለት

.. ልብ ያለው አገሩ ሰማይ ነው

.. ልብ ያሰበውን አፍ ይናገራል አይን ያየውን እጅ ይሰራል

331. መሱንታመ ከነይ አሳ ሰጤስ

. ቁስላም ውሻ ሰው ይነክሳል

.. ለሰበበኛ ቂጥ በርበሬ አታሳዩት

.. ሆድ ለባሰው ማጭድ አታውሰው

332. መሱዋ ኩሽየን ዎገ ጎሲ አዴስ

. ቀላዋጭ ትልቅ ቅል ይይዛል

.. ጨኸት ለቁራ መብሉ ላሞራ

.. የሰው ወርቅ አያደምቅ

333. መስቀለ ምታ ቁርኪ ጊዳኔ ገዝያ ከሴት ኤቁስ

. የመስቀል እንጨት አልፈልጥም ብሎ የተኛው በጨዋታ ቀን ከሰው ቀድሞ ይቆማል።

.. እንካን የማያውቅ አምጣን ማን አስተማረው

.. ቱሪናፋ ቱሪናፋ ከጦር ሜዳ አትገኝ ከገበታ አትጠፋ

334. መስቀለው ማዩኑ ማዩዋ ተመይ ሞ

. ለመስቀል ያልተለበሰ ልብስ እሳት ይብላው

.. ለመስቀል ያልሆን ቀሚስ ይበጣጠስ

.. ለጥምቀት ያልሆን ቀሚስ ይበጣጠስ

335. መስቀለው ቆሬ ሰክዮጌኔ በዴሰው ኩሼ ሰክዮጌ እሱወ

. በመስቀል ጉረሮ መታመምና በአዝመራ (መከር) ወቅት እጅ መታመም አንድ ነው

.. ሳር ሲበቅል ፈረስ ይሞታል

.. ያልታደለ አሞራ አንበጣ ሲመጣ አይኑ ይታወራል

.. ያልታደለች ወፍ በጥቅምት አይኗ ይጠፋል

336. መስቀለው ዩደ ጊለእያ ዴአይ ሀጋ ገውሱ

. ለመስቀል የመጣች ሙሽራ ኑሮ እንዲህ ነው ትላለች

.. በመስቀል የተገዛች ባሪያ ሁል ጊዜ መስቀል ነው ትላለች

337. መሸኩወን ካአነ ጊኮ መረ ሄንተይ አቶ

. በሽርጥ ትጫወት እንደሆን ጥጃ ማገዱ ይቅር

.. ቀልድና ቅዘን ቤት ያጠፋል

338. መቆይ በይነ ከዎይ እስ ለይተፔ ደሮ ከዎቴነ

. መካሪ የሌለው ንጉስ ያለ አንድ አመት አይነግስ

.. መካር የሌለው ንጉስ ያለ አንድ አመት አይነግስ

339. መተ ቦሎይ ዎጠን ኡቴስ

. በቅርብ ያለ አማች ወፍጮ ላይ ይቀመጣል

.. አወቅሁሽ ናቅሁሽ

.. አብሮ መኖር ያናንቃል

340. መተይ ቀረጠ አሼነ

. ቅርበት ከቀረጥ አያድንም

.. ያልጠረጠረ ተመነጠረ

.. ምንም ቢዋደዱ ባዕድን አይረዱ

.. አይመጣምን ትተሽ ይመጣልን በጨመርሽ

341. መችያ ማሬሆ ግን፣ አዝነይ ሼኔሆ ግን ካሬ ከነው አቴስ

. ሚስት እንጃልህ ስትል ባል እንጃልሽ ሲል ቤት ለውሻ ይቀራል

.. የፉክክር ቤት ሳይዘጋ ያድራል

342. መችያ ማሬኮ ግን፣ አዝነይ ሼኔሆ ግን ኪተይ ከናስ አቴስ

. ሚስት የራሱ ጉዳይ ስትል ባል ቸል ሲል ቤቱ ለውሻ ይቀራል

.. የፉክክር ቤት ሳይዘጋ ያድራል

343. መችያ አያኑ! ግን ጦስ አቲስ ጌስ

. መልካም ጋብቻ ይሁንልህ! ቢለው እግዚር ነው እንዲህ ያደረገኝ ይላል

.. ፍየሏ ወዲህ ቅዝምዝም ወዲያ

.. ያልሰማ ጆሮ ከጐረቤት ያጣላል

344. መችያ እንዴሽን ሆኡዋ ቆምቱ ገውሱ

. ሚስት አሮጊት ነች ግን ትሞቃለች

.. ኑሮ ካሉ መቃብር ይሞቃል

.. የሰው ከመመኘት በራስ መኩራት

.. የሰው ከማየት የራስን መብላት

.. የሰው ወርቅ አያደምቅ

345. መችያ ከትን ማነ ጌስ ኩቶይ

. ሚስቴ ሰርታልኝ እበላለሁ ይላል ዶሮ

.. ወግ ነው ሲዳሩ ማልቀስ

.. ሲሉ ሰምታ ዶሮ ታንቃ ሞተች

.. ሲወልዱ አይታ በጠጧን ጣለች

346. መችያ ዎርዶጋ ኦለይ ዎሬስ

. ሚስቱ የገደለችውን ጦርነት ይገለዋል

.. የተከፋ ተደፋ

347. መችያ ጎበደ ኪታወ ወደውሱ

. ሚስት ካየለች ባሏን ትደበድባለች

.. ይህቺ ባቄላ ካደረች አትቆረጠምም

.. አሽከር ሲበረታ (ሲያይል) ጌታውን ያዛል

348. መችዮ እጥየ ኡር ናቱፔ አቴስ

. ሚስት የሚጠላ ወንድ ያለ ልጅ ይቀራል

.. ያልጠረጠረ ተመነጠረ

.. አይመጣን ትተሽ ይመጣልን በጨመርሽ

.. ሁለት ወዶ አይሆንም

349. መችዮ ኤክን ሜቶይ ሶሬፔ፤ ቦሎሶፔ እመተይ፤ ዘምባ ጠለሄ ሻፋፔ፤

. ሚስት ሲያገቡ ችግር ከሶሬ፤ ከቦሎሶ እንግዳ፤ የዘምባባ ቆሌ ከወንዝ

.. ወደሽ ከተደፋሽ ቢረግጡሽ አይከፋሽ

.. መከራ ፈንጣጣ የሽምብራ ቂጣ

.. ከበሮ በሰው እጅ ያምር ሲይዙት ይደናገር

350. መችዮ አይቼናኔ ላዘንታ ዬዴስ

. ሚስት ያላጨ አማጭ (ሽማግሌ) ይልካል

.. ወጡ ሳይወጠወጥ ወስከምቢያው ቁጢጥ

351. መችዮ ወዴነ አገነይ ኡዱለ ምታ ቶኪስ

. ሚስቱን የማይመታ ባል ዘነዘና ያነሳል፤ (ይሸከማል)

.. ላያውቁሽ ታጠኝ

.. ሲሉ ሰምታ ዶሮ ታንቃ ሞተች

.. ከማን አንሼ

.. ፈሪ እንዳይሉ አንድ ገደልሁ፣ ጉበዝ እንዳይሉ አልደገምሁ

352. መችዮኔ ነአኔ ከልሰነው ዴምባ ኦተ፣ ቦሎትዮ ቤሰነው

ላንቅያ ኦተ

. ሚስትና ልጅ ለማጥገብ ሜዳ እረስ አማትን ለማሳየት ሸለቆ እረስ

.. ጥቅምና ይሉኝታ አብረው አይሄዱም

.. የሚበጀውን ባለቤቱ ያውቃል

.. ኑሮ በመላ

353. መችፔኔ ሚዛቪኔ አው ሺኔ ከልስያብ ባወ

. ከሚስትና ከላም ሌላ ፍላጐትን የሚያረካ የለም

.. ምንም ቢያርሱ እንደ ጉመን አይጐርሱ

.. ካለፈቱ አይቆርሱ ካለርስት አይወርሱ

354. መቹን ሀንቴትድ አዋ ሆአነ ጊድ ክይደ ኤጬርያ ጥንግሌ ኤኪስ

. በሚስቱ ተናዶ ፀሐይ ለመሞቅ ውጪ የወጣውን አይጥ ጭልፊት ይወስደዋል

.. የተከፋ ተደፋ

.. አተርፍ ባይ አጉዳይ

355. መቾ ወደ ግን ሹጎ ወዴስ

. ሚስትህን ደብድብ ቢሉት ደካማን ይደበድባል

.. የምታሸንፈው ቢባል ወደሚስቱ ሮጠ

356. መነ አይያ መ ስመደ ላቁሜተይስ ገውሱ

. የማና እናት ከበላች በኋላ እያላመጥኩ ነኝ ትላለች

.. ሞኝ አያውቁብኝ ባይ

.. ላያውቁሽ ታጠኝ

357. ... ኩቶይ ኦጌን ኡትድ ኡዱሳ መሲስ

. ኩቲ የተበላ ሸክላ ሰሪ መንገድ ላይ ተቀምጦ ሙቀጫ ይጠርባል

.. አያገባው ገብቶ አያወዛው ተቀብቶ

.. ያለቦታው የገባ

358. ... ሜድ ሜዲድ ቦንአን ሜስ

. ሸክላ ሰሪ ሰርቶ ሰርቶ በገል ይበላል

.. ለፍቶ መና

359. ...ግትያ (ፕርየ) ኤርን ጌንእያ ገፋ ኢረውሱ

. ሸክላ ሰሪ ማጥመድ ሲያውቅ ሚዳቋ መዝለል ታውቃለች

.. ብልጥ ለብልጥ አይን ፍጥጥ (ብልጥጥ)

.. እባብ ለእባብ ይተያያል ካብ ለካብ

360. ...ጥንቀተው ማይዮ ማዮይ ቦተ ጨርቀ

. ሸክላ ሰሪ ለጥምቀት የሚለብሰው ልብስ ነጭ ቡትቶ ነው

.. ሲሉ ሰምታ ዶሮ ታንቃ ሞተች

.. የድሃ ነገር ማንገቻ የለውም

361. ...ጭሚድ ሙሽ ቆጢስ

. ቀጥቃጭ ሲያረጅ ዱልዱም ይቀጠቅጣል

.. ካረጁ አይበጁ

.. አንበሳ ሲያረጅ የዝንብ መጫወቻ ይሆናል

362. ...መቅዶ መጫስያ አዴ ጭማ ጌለውሱ

. ጠይብ የመከራት ሴት ሽማግሌ ታገባለች

.. ሞኝ እንደመከሩት

363. ...ሱቅን ማንቴሎይ ደዴስ

. ሸክላ ሰሪ የፈተለችውን ማንቴሎ ይሰራል

.. ግም ለግም አብረህ አዝግም

.. ቂጢኛም ከውርጄ ይዞራል

364. መንቅስነ መችያ መጥንያደን መልአውሱ
. የምታደኸይ ሴት እንደጨው ትጣፍጣለች
.. ከፉ ሴት ጥዋት ወተት ማታ ሬት
365. መንቅስነው ጮንቼስ
. ሊያደኸይ ሲል ሆዳም ያደርጋል
.. የሚፈርስ ከተማ ነጋሪት ቢመታ አይሰማም
.. ያልጠረጠረ ተመነጠረ
.. የዘፈን ዳር ዳሩ እስክስታ
366. መንቅዳኒ ዱሬተነባኔ ቢዳኒ ያነባኔ አስ ኤሪ?
. የደኸየ እንደሚከብርና የሄደ እንደሚመለስ ሰው ያውቃልን?
.. ለሁሉም ጊዜ አለው
.. ቀን እስኪያልፍ ያለፋል
.. ማወቅ መላቅ አለማወቅ መናቅ
.. አይመጣምን ትተሽ ይመጣልን በጨመርሽ
.. ያልጠረጠረ ተመነጠረ
367. መንቄተነ ቆሬ ኡብ ዎዴ መልአባ አሞቴስ
. የሚያደኸይ ጉረር ሁሌ ባፉጭ ነገር ይመኛል
.. ሆዱን የወደደ ማእረጉን ይጠላል
.. ሆዱን ያለ ሆዱን ተወጋ
368. መንቆ መቶይ ጎሽ ዛሬስ
. የድህነት ስካር አሳብዶ ይመልሳል
.. ቀን ያልፋል እስኪያልፍ ያለፋል
.. መከራን የቻለ አሸናፊ ነው
369. መንቆ ኩሽየን መረጨ አዴስ
. ደሀ አንጀት ይደርሰዋል
.. ይታደሏል እንጂ አይታገሉም

370. መንቆቴተይ ጎሻ ኤርሲስ፣ ቀሾይ ሞቶ ኤርሲስ

. ድህነት እርሻ ማረስ፣ እስራት ሙግት ያሳውቃል

.. ዳን ላለው መድኃኒት አለው

.. ችግር ብልሃትን ታስተምራለች

371. መንቆይ መንድሽን ዱሬ ም ካሌስ

. ድሃ ሲገዛት ሀብታም እየበለፀገ ይሄዳል

.. ድሃና ጌታ ተሟግቶ ድንጋይና ቅል ተማትቶ

.. ምንም ብታፈገፍጊ ከግድግዳ አታልፊ

372. መንቆይ ደንጩዋ ጊግስሽን ሞቶይ አቴስ

. ደሃ እስከ ሚለባብስ ሸንጐ ይበተናል

.. ድሃ ሲቀማጠል ከወገቡ ቅምጥል

.. ሲያጋጌጡ ይመላለጡ

373. መንቆይ ዱርየን ላሜቴነ

. ድኽነት በሀብታምነት አይለወጥም

.. ምኞት ያከሳል

.. ከመመኘት መስራት

374. መንቆይ ዲሽን ሜሄ ደሪስ ጎፐ

. ድህነት እያለ ሀብት በዛ አትበል

.. አይመጣምን ትተሽ ይመጣልን በጨመርሽ

.. ያልጠረጠረ ተመነጠረ

375. መንቆይ ጦሳ ጨዩስ

. ድሃ እግዚአብሔርን ይሳደባል (ይራገማል)

.. ይታደሷል እንጂ አይታገሉም

376. መንቆይ ፐጠነ ጊድ ፕላ ላጤስ

. ድሃ ያልፍልኛል ብሎ አይብ ምሳ ይበላል

.. ላይቀር ሞቱ መንጠራራቱ

.. እግዜር ያለው ላይቀር አንዴ የወሰነው፣ መጨነቅ መጠበብ እንዲያው በከንቱ ነው

377. መንእየን ጎፍንያ ድግዶጌ ሶ ቢድ ጌዳፔ ፐረ ዬደ ጌስ

. በወቅቱ ሳንባ የነሱት እቤት ሄዶ ታናሽ ታላቅ ቆርጠህ ላክ ይላል

.. ላያውቁሽ ታጠኝ

.. ሄዳ ጉበት ይነሷታል ታላቅ ታናሽ ስደዱልኝ አለች

378. መንጋገይ መልኦ ቤእን ቅንጣሌ በቀ ኤኬስ

. መንጋጋ ጣፋጭ ሲያገኝ ጉንጭ በጥፊ ይመታል

.. ለሃጥአን የመጣ ለፃድቃን ይተርፋል

.. አይጥ በበላ ዳዋ ተመታ

379. መንጋግ መልኦ ኤክን ሸከል በቀ ኤኬስ

. መንጋጋ ጣፋጭ ሲበላ ጆሮ ግንድ ጥፊ ይቀምሳል

.. አይጥ በበላ ዳዋ ተመታ

380. መከላ ማረሸይ ጎዬነን ሻጬስ

. የልግመኛ ሰው ማረሻ ሳያርስበት ይከርማል

.. ወስፌ ሲለግም ቅቤ አይወጋም

381. መከላፔ መንቆይ ኬሀ

. ከልግመኝነት ድኽነት ይሻላል

.. ልቤ ንፁህ ሆኖ ባቴ ደም ብቻ ይሁን ትላለች ልጃገረድ

.. ክፉ ለራሱ

382. መከራረ አዝነይ መጥሽን ቢድ ጠውህሽን ዬስ

. የሰነፍ ሴት ባል ጐመን ስትቀነጥስ ሄዶ ስትቀረድድ ይመጣል

.. ከሞኝ ቤት እንግዳ ይናኝ

.. ሰነፍ ሴት ያገባ በሬው በሰኔ ገደል የገባ

383. መዝየው ተልኤስ፣ ማዩወው ኖሬስ

. እንስት አይቶ ያበድራል፣ ልብስ አይቶ ያከብራል

.. ላለው ቅንጭብ ያረግዳል

.. ገንዘብ ከጅ ዘመድ ከደጅ

384. መይ መላፔኔ ዎልቃፔኔ ጠዩነ

. የበላ ወይ ከመልክ ወይም ከጉልበት አንዱን አያጣም

.. የበላ በለጠኝ፣ የሮጠ አመለጠኝ

.. የበላ ከሰውነቱ የተቀባ ከፊቱ

385. መይ መልአ ማየይ ሆአ ኤሬስ

. የበላ ጣዕሙን ያውቃል የለበሰ ሙቀቱን ያውቃል

.. ያየ ይናገር የገደለ ይፎክር

.. ሺ ጊዜ ከመስማት አንድ ጊዜ ማየት

386. መገና መይ መንቁስ

. አደራ የበላ ይደኸያል

.. አደራ ጥብቅ ሰማይ ሩቅ

.. የተናገሩት ከሚጠፋ የወለዱት ይጥፋ

387. መገንጦይ ቱማ አሼነ ጌስ

. በጉቦ እውነት አይሸፈንም አለ

.. እውነትና ንጋት እያደር ይጠራል

388. መጋዩስ ሄዘንቶ ኪተይ ሀይቆ

. ለባዝራ ሶስተኛ ቤት መሞቻዋ ነው

.. አለማገረፍ ጣር ያበዛል

.. እግር ሄዶ ሄዶ ካር ጉድጓድ ይገባል

389. መጠይ ዴእሸን ጤለይ ሜስ

. ያፈራ እያለ ያየ ይበላል